
# ባብ

## የአዲሱ ዘመን አብሳሪ




ባብ የተወለደው ኦክቶበር 20 ቀን 1819 በኢራን ደቡባዊ ክፍል በምትገኝ ሺራዝ በምትባል ከተማ ነበር። አባቱ ሲሞት ገና ልጅ ነበር። ያደገው በአጎቱ ሲሆን በለጋነቱ ትምህርት ቤት አስገብቶታል።




የባብ መምህር ታላቅ ችሎታውን በፍጥነት ተገንዝቦ እንደዚህ ዓይነት ልዩ የሆነ ልጅ ማስተማር እንደማይችል ተገነዘበ። ባብ የተፈጥሮ እውቀት በእግዚአብሔር ተሰጥቶታል።



በዚያን ጊዜ የኢራን ሰዎች አዲሱን የእግዚአብሔር መልእክተኛ መምጣት ይጠባበቁ ነበር። በምድር ላይ ሰላምና ፍትህ እንዲመጣ በቅርቡ እንዲከሰተ ጸለዩ። ብዙዎች ተስፋ የተገባለትን መልዕክተኛ ፍለጋ ቤታቸውን ፍለጋ ተሰማሩ።




ሜይ 23 1844 ዋዜማ አንድ ወጣት ቃል የተገባውን ለመፈለግ ሺራዝ ደረሰ። ባብ ከከተማው በር ውጭ አገኘው እና ከረጅም ጉዞው በኋላ እረፍት እንዲያደርግ ወደ ቤቱ ጋበዘው። ከዛም ባብ በጉጉት ሲጠባበቅ የነበረው እርሱ መሆኑን አወጀ።



“ባብ” የሚለው ቃል “መግቢያ” ወይም “በር” ማለት ነው። ባብ ሁሉንም የዓለም ህዝቦች በማሰባሰብ
አንድ ቤተሰብ የሚያደርግ ሌላ የእግዚአብሄር መልእክተኛ እንደሚመጣ አውጇል።
ባብ የሰውን ልጅ ወደ አዲስ እና የከበር መጪው ዘመን እንደሚመራ በር ነው።



የባብ ተከታዮች ቁጥር በፍጥነት አደገ። በመላው ኢራን ውስጥ እርሱ የከሰተውን መለኮታዊ ትምህርቶች ማሰራጨት ጀመሩ።



ብዙም ሳይቆይ በሕዝብ ላይ ሥልጣናቸውን እንዳያጡ የፈሩት የመንግሥት ባለሥልጣናትና ቀሳውስቱ በአዲሱ የአምላክ እምነት ላይ ተነሱ። ባብን ከተከታዮቹ አርቅው በሀገሪቱ ጫፍ በሚገኝ የምሽግ እስር ቤት ውስጥ አሰሩት።



የባብ ተከታዮች እጅግ በጣም የከፋ ስቃይ ደረሰባቸው። ተጠቁ፣ ተደበደቡ፣ ለእስራትም ተዳረጉ። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር እምነት መስፋፋቱን ቀጠለ።



በ1850 ባብ ሰማዕት ሆነ። በመንግስት ትእዛዝ መሠረት ከአንድ ተከታዮ ጋር በአንድ ግቢ ውስጥ በገመድ ከግንድ ጋር ታሰረ እናም በወታደሮች ስልፈኛ ተረሸነ። ባብ ሲሰዋ 31 ዓመቱ ነበር።



ባብ ህይወቱን የሰጠው "የእግዚአብሔር ክብር" የሆነው ባሃኡላህ፣ የእምነቱ ሰንደቅ በሁሉም የፕላኔቷ ማዕዘናት ላይ እንደሚውለበለብ አይቀሬ ለሆነው መምጣት መንገድ ለማዘጋጀት ነው ።

Copyright © 2007, 2023 by the Ruhi Foundation, Colombia
All rights reserved. Edition 2.1.1.PE. May 2023, published in Amharic

Ruhi Institute
Email: instituto@ruhi.org
Website: www.ruhi.org